# በእስራኤል የመሬት መንቀጥቀጥ ይከሰት ይሆናል በማለት ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ሊያስከትል የሚችለውን ከፍተኛ የህይወት ጥፋትና የንብረት ውድመት

አስመልክቶ የተሰጠ መንግስታዊ ምግለጫ።

ለወደፊቱ በእሥራኤል የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ከመድረሱ በፊትና ከደረሰም በኋላ ምን ዓይነት ጥንቃቄ

መውሰድ እንደሚገባ የተሰጠ መመሪያ።

ከአሁን ቀደም በአካባቢያችን ከፍተኛ ጥፋት ያደረሰ የመሬት መንቀጥቀጥ ተከስቶ እንደነበር የሚታወስ ቢሆንም፤ ለወደፊቱም ከባድ ተመሳሳይ አደጋ በአካባቢያችን እንደሚከሰት ጠበብቶች ያስጠነቅቃሉ ።

ይህ የተፈጥሮ አደጋ መቸና በምን ሰዓት እንደሚደርስ አስቀድሞ በትክክል መተንበይ ባይቻልም በእሥራኤል ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትል የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ መድረሱ አይቀሬ በመሆኑ አስቀድመን ተገቢውን ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል።

## የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን?

ከአሁን በፊት አልፎ አልፎ በተከሰቱት መጠነኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ነውጦች ፣ ወለሉ ሲንቀጠቀጥ ፣ መስኰቱ ሲናወጥ፣ የቤት ዕቃዎችና የኤሌክትሪክ መብራቶች ሲወዛወዙ አይተናል ።

## የመሬት መንቀጥቀጡ አደጋ በደረሰ ጊዜ ማድረግ ያለብን ተገቢ መንገድ።

***አደጋው ሲደረስ በህንጻ ወይም በቤት ውስጥ ከሆናችሁ፤ በሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች በፍጥነት ወደ ገላጣ ቦታ መሄድ አለባችሁ።***

1ኛ. በፍጥነት ወደ ገላጣ ቦታ ውጡ - ይህም ከህንጻው የመውጣት እድል ካለ ማለት ነው። ይህ የሚሆነው በምድር ቤት የምትኖሩ ከሆነ ብቻ ነው።

2ኛ. ከአደጋው ሊከላከልላችሁ ወደ እሚችል ቦታ ግቡ (ሜማድ) ወይም በመወጣጫ ደረጃዎች ተቀመጡ። እንዳጋጣሚ በፍጥነት ወደ ውጭ መውጣት ካልተቻለ እዚያው እቤታችሁ ውስጥ ባለ የአደጋ ጊዜ መከላከያ ክፍል ግቡ። ይህ ከሌለ የጋራ መጠቀሚያ ሚቅላጥ ውስጥ መግባት ወይም ከቤቱ ደረጃ (ማድረጎት) በመቀመጥ አደጋው እስኪያልፍ ድረስ መጠበቅ።

3ኛ. ጊዜ ካልተገኘ ግን በቤታችሁ ውስጥ ጠንካራ ጠረጴዛ ካለ ወይም ከመካከለኛው ክፍል (ኸደር) ውስጥ መግባት ያስፈልጋል ።

***ተጨማሪ መመሪያ፦ አደጋው በደረሰ ጊዜ በማንኛውም አይነት ህንጻ ውስጥ ካላችሁ፤***

* ከዋናው ግንብ በውጨኛው ክፍል ከመስኰቶችና ዕቃ መደርደርያ ካለበት አካባቢ መራቅ፤

* መሬት በሚንቀጠቀጥበት ጊዜም ሆነ ካበቃ በኋላ በመዓሊት መጠቀም ክልክል ነው። ምክቢያቱም ውስጥ እያላችሁ ማዕሊቱ ሊበላሽና የበለጠ ችግር ሊደርስባችሁ ይችላልና።

* ምን አልባት በተሽከርካሪ ወንበር (አጋላ) የሚጠቀም ሰው ቢኖር መጠለያ ቦታ ከደረሰ በኋላ ተሽከርካሪው ጐማ እንዳይንቀሳቀስ በመቆለፍ እራሱ እንዳይጎዳ መከላከል፤

* **በአጋጣሚ ከቤታችሁ ውጭ ከሆናችሁ** ከግንብ፣ ከድልድይና ከኤሌክትሪክ ምሰሶዎች አካባቢ መራቅ፤

* **ከባህር ዳርቻ አካባቢ የምትገኙ ከሆነ** በአስቸኳይ አካባቢውን ለቅቃችሁ መውጣት አለባችሁ። ምክኒያቱም ከፍተኛ የባህር ሞገድ ማለትም (ጹናሚ) ተነስቶ አካባቢውን ሊያጥለቀልቀው ይችል ይሆናል። ከመሬት መንቀጥቀጡ በኋላም ወደ ባህሩ ዳርቻ መመለስ ተገቢ አይደለም።

ማሳሰቢያ፦ በት/ቤትና በመዋዕለ ሕጻናት (ጋን ይላዲም) በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ ስለሚደረገው ቅድመ ጥንቃቄ የት/ሚኒስቴር በልዩ ሁኔታ መመሪያ ይሰጣል።

## አደጋው ከደረሰ በኋላ የሚደረጉ ተገቢ ጥንቃቄዎች፤

* እሳት ማቀጣጠልና የኤሌክትሪክ ማብሪያና ማጥፊያ መጫን (በእጅ ስልክ መጠቀም) ተገቢ አይደለም፤ ምክኒያት ለጋዝ ፍንዳታ መንስኤ ይሆናሉ ተብሎ ስለሚሰጋ ነው።
* ከቤት ወጥታችሁ ራቅ ወደ አለ ገላጣ ቦታ በመሄድ እዚያው መቆየት።
* ከቤት ወጥታችሁ ከመሄዳችሁ በፊት የጋዝ ቧንቧውንና ዋና የኤሌክትሪክ ቆጣሪውን መዝጋትና ማጥፋት አለባችሁ።

## ከፍርስራሹ ውስጥ ከእነ ህይወታቸው የተቀበሩ ሰዎች ካሉ ?

* በአላችሁበት ቅርብ አካባቢ ከፍርስራሹ ውስጥ የተቀበሩ ሰዎች ካሉ፤ ተገቢውን የእራስ ግምት በመውሰድ እንደ ረዥም ብረት እና ትራክተር በመጠቀም ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ከባድ ነገሮችን በማንሳት ለተጎጅዎች እንደ አስፈላጊነቱ የመጀመሪያ እርዳታ ማቅረብ መልካም ነው።
* **ተጨማሪ የመሬት መንቀትቀጥ:-** ወዲያውኑ በደቂቃ ውስጥ ወይም በሚቀጥለው ቀን ለሁለተኛ ጊዜ የመሬት መንቀጥቀጥ ድጋሚ ሊደርስና ቀደም የተጐዳው ሕንጻ በቀላሉ ሊደረመስና ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል፤ ነፍስ ለማዳንና አስቸኳይ እርዳ ለመስጠት ካልሆነ በስተቀር ወደፈራረሰው ሕንጻ መግባት አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ከወዲሁ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## የመሬት መንቀጥቀጥ ከመድረሱ በፊት ሊደረጉ የሚገባቸው ቅደመ ዝግጅቶች

### የህንጻው ጽኑኔና ጥንካሬነት

የምትኖሩበት ቤት ጥንካሬውና ጽኑነቱን ለማወቅ በእስራኤል የቤቶች ስነ ግንባታ ህግ መሰረት (413)

አስቀድሞ ባለሙያ መሃንዲስ አስመጥቶ ማስመርመርና ጥንካሬውን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

አብዛኛው ቤቶች የተሰሩት ከ 1980 ዓ.ም በፊት በመሆኑ የጥንካሬ አቅማቸው ደካማ ሊሆን ስለሚችል፤

የሃገሪቱ ሕግ እንደሚፈቅደው ቤት እድሳትን አስመልክቶ መንግስት በወጬ ስለሚተባበር እርዳታውን ለመቀበል ማመልከቻ ማቅረብ ያስፈልጋል።

የቤቶችን እድሳት በተመለከተ ተጨማሪ መመሪያና ማብራሪያ በኢንተርኔት

www.moin.gov,il/tama 38 ማግኘት ይቻላል፤ ስለዚህ አንድ ቤተሰብ አስቀድሞ ለችግሩ መፍትሔ

በመፈለግ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል።

ሁሉም ሰው ለችግር ጊዜ የሚሆን ደረቅ ምግብ ፣ ውሃ ፣ ራዲዮ ፣ የእጅ ባትሪ ፣ አስፈላጊ የሆኑ የሕጻናት

መገልገያ ዕቃዎችን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፤ ምን አልባት አደጋ ቢደርስ ቤተሰቡ ሊጠለልበት የሚችል አስተማማኝ ቦታ ወይም ሚቅላጥ የመሳሰሉት ሁሉ በአካባቢ መኖራቸውን አስቀድሞ ማጥናትና ማወቅ አለበት፤ እንዲሁም በአደጋ ጊዜ ቤተሰቡ ሊለያይ ስለሚችል የሚገናኙበትን ቦታ አስቀድሞ ከቤተሰቡ ጋር

ተመካክሮ መወሰን ያስፈልጋል ።

በዚህ መንግሥት በሰጠው መመሪያ መሠረት እያዳንዱ ቤተሰብ ምን አልባት ሊሆን ይችላል ብሎ

መጠንቀቅና መዘጋጀት ይኖርበታል።

**ለተጨማሪ ማብራሪያ-** የመሬት መንቀጥቀጥ ቅደመ ዝግጅት በኢንተርኔት:- www.egred.gov.il ወይም የደጀን ዕዝ መምሪያ በኢንተርኔት www.oref.org.il ወይም በስልክ 1202 ጠይቆ መረዳት ይቻላል።